# የአማራ ፋኖ ድምፅ
# The Voice of Fano

በወቅታዊ አርዕስት በአፋሕድ የፖለቲካ ጉዳዮች መምሪያ እየተዘጋጀ የሚቀርብ
Issued by AFPO Department of Political Affairs on Current Topics

Vol. 1; No. 2
አንደኛ ዓመት ሁለተኛ ቅጽ

Wednesday, August 27, 2025
ረቡዕ ነሐሴ ፳፩ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም.

## ርዕሰ አንቀጽ

### የጦርነትና የግጭት ቀጠና በሆኑ አካባቢዎች ለሰብዓዊ መብቶች መከበር እና ለዜጎች ደኅነንት የቀረበ የትብብር ጥሪ

የሰው ልጆች የሰብአዊነት መርሆች እንዲከበሩ የሚያስችሏቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያደረጉ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አንዱ እና መሰረታዊ የሆነው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ (Universal Declaration of Human Rights) /UDHR/ ነው። በዚህ ዓለም አቀፍ ድንጋጌ መሠረት ማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር ሰው በመሆኑ ብቻ ያገኛቸውን በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደኅንነት፣ የነፃነት መብት እና ከማንኛውም ኢ- ሰብአዊ አያያዝ የሚጠበቅ መሆኑን ይደነግጋል። ይህን ሕግ ማንኛውም የኅብረቱ አባል ሀገራት የማክበርና የማስከበር ግዴታ እንዳለባቸው በድንጋጌው ተጠቅሷል።









### አሁናዊ የሰብዓዊ መብት ሁኔታ በኢትዮጵያ

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ዘርፈ ብዙ ሰብዓዊ መብት ጥሰት እየተፈጸመ ይገኛል። በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ብሄርን፣ ኃይማኖትንና አካባቢን መነሻ በማድረግ አገዛዙ በሚፈጥረው ግጭት የዜጎች ደህንነት አደጋ ውስጥ እየወደቀ ይገኛል።

የአብይ አሕመድ አገዛዝ ወደ ስልጣን ከመጣ ጊዜ ጀምሮ በተለይም ባለፉት ሁለት አመታት በኢትዮጵያ ውስጥ በሕይወት የመኖር መብት፣ ከቦታ ቦታ በነጻነት የመንቀሳቀስ መብት፣ በጥበቃ ሥር ያሉ (የታሰሩ) ሰዎች የሰብአዊ መብቶች አያያዝ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብቶች፣ የሴቶች እና የሕፃናት መብቶች፣ የስደተኞች፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ያሉበት ሁኔታ ከየትኛውም ጊዜ በላይ አሳሳቢ እየሆነ መጥቷል። በተለይም የአማራ ማንነት ያላቸውን ዜጎች አገዛዙ በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ከቀያቸው እንዲነቀሉና በየቀኑ ጥቃት እንዲደርስባቸው እየተደረጉ ይገኛል። ባለፉት ጥቂት አመታት ብቻ በአዲስ አበባ ዙሪያ የኮሪደር ልማት ሰበብ ከመቶ ሺህ በላይ የሚሆኑት እንዲፈናቀሉ ተደርጓል። ከኦሮሚያ ክልል ብቻ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የአማራ ተወላጆች ተፈናቅለው አብዛኞቹ የሚያሰባስባቸው ጠፍቶ ተበትነው የቀሩ ሲሆን ወደ ካምፕ የገቡትም ለርሃብ፣ ለበሽታ፣ ለአዕምሮ ጭንቀትና ልዩ ልዩ በሽታ ተጋላጭ እንዲሆኑ ተደርገዋል።

### በአማራ ህዝብ ላይ በተለየ ሁኔታ ያነጣጠረው የዘር ማጥፋት ወንጀል

በጦርነት አውድማ ውስጥ የሚገኘው የአማራ ህዝብ፣ በአገዛዙ ማን አለብኝነት ከፍተኛ የሆነ የሰብዓዊ-መብት ጉዳት እያስተናገደ ይገኛል።

ከከተማ እስከ ገጠር ድረስ በሜካናይዝድ ጦርነት ተከፍቶበት ከፍተኛ ግፍ እና በደል እየደረሰበት የሚገኘው የአማራ ህዝብ፣ በሰላም ውሎ መግባቱ ቅንጦት ሆኖበታል። የሰብዓዊ መብት ጉዳይም በእጅጉ አደጋ ውስጥ ወድቋል።

በቅርቡ አፋሕድ ባሰባሰበው መረጃ መሠረት በክልሉ ውስጥ ባሉ ሁሉም ወረዳዎች ጦርነትን ሰበብ አድርጎ በንፁኃን ላይ የሚፈፀሙ የድሮን ጥቃቶች፣ ከሕግ ውጪ የሚፈፀሙ ግድያዎች፣ በሲቪል ሰዎች ላይ ያነጣጠሩ ጥቃቶች አስደንጋጭ ደረጃ ላይ መድረሱን ተመልክቷል። ይህን መረጃ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽንም በመጠኑም ቢሆን ጥናት አካሂዶ አረጋግጧል። ከግድያ ባሻገር የመሰወር፣ የጅምላ እስር፣መንገድ ላይ እንዲሁም ከቤት ውስጥ አፍኖ በመውሰድ በከፍተኛ ገንዘብ መደራደር እና በማናለብኝነት ይዞ የማቆየት አልፎ አልፎም ሕይወታቸውን የመቅጠፍ ተግባር በከፋ ደረጃ ቀጥሏል።

የእንግሊዙ ዓለም አቀፍ ሚዲያ BBC የአውሮፓ የፍትሕና ሕግ ማዕከል የተባለ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅትን ጠቅሶ እ.ኢ.አ በ2024 ባወጣው ሪፖርት “ድምጽ አልባው የአማራ ሕዝብ ስቃይ በኢትዮጵያ” በክልሉና ከክልሉ ውጭ ከ2010 ዓ.ም. ጀምሮ የተፈጸሙ ጥቃቶችን ዘርዝሯል። በበርካታ የኦሮሚያ ክልል እና በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች ትንንሽ ምክንያቶችን ሰበብ በማድረግ በብዙ ሺህ የሚጠቀሱ አማራዎች ለግድያ መዳረጋቸውን ሚዲያው ያትታል።

በተጨማሪም የአማራ ማህበር በአሜሪካ (Triple A) ባወጣው ሪፖርት መሰረት የድሮን ጭፍጨፋ በገበያ፣ በትምህርት ቤት እና በጤና ጣቢያ የተገኙ በጦርነት ተሳታፊ ያልሆኑ በርካታ ንፁኃን የተገደሉ ሲሆን ለአብነትም ከመስከረም 15 እስከ ታኅሣሥ 21 ቀን 2017 ዓ.ም በአማራ ክልል በሚገኙ 46 ወረዳዎች በተደረጉ 99 የሰው-አልባ አውሮፕላኖች እና የአየር ድብደባዎች 390 ሰዎች ሲሞቱ 135 ቆስለዋል በአጠቃላይ 525 ሰዎች ላይ ጉዳት መድረሱን መዝግቧል። ይህ ጉዳት የደረሰ በሶስት ወር ውስጥ ሲሆን በሁለት ዓመት ጦርነት ውስጥ የደረሰው ጉዳት ምን ያህል እንደሆነ ለመገመት አያዳግትም።

እንዲሁም በአማራ ክልል ሪፖርቱ በተጠናቀረባቸው ዞኖች ብቻ እስከ ሀምሌ 2016 ዓ.ም የደረሰውን ጉዳት፡-

- 269 ሰዎች ላይ አስገድዶ መድፈር ጥቃት የተፈፀመ ሲሆን የዚህ ወንጀል ሰለባዎች አብዛኛዎቹ ወጣት ልጃገረዶችና ሴቶች ሲሆኑ በጥቂቱ ወንድ ቄሶች እና ወጣት ወንዶችም ሰለባ ሆነዋል፣

## Editorial

### A call for cooperation for the respect of human rights and the safety of citizens in war and conflict zones

Humans have made international agreements that allow them to respect the principles of humanity, and one of the most fundamental of these is the Universal Declaration of Human Rights (UDHR). This international declaration states that every human being is entitled to the rights to life, security of person, liberty and freedom from inhuman or degrading treatment by virtue of being human. The declaration states that all member states of the Union are obliged to respect and uphold this law.

#### Current Human Rights Situation In Ethiopia

Ethiopia is currently experiencing widespread human rights violations. The security of citizens is at risk due to the conflict that the regime has created in various parts of the country based on ethnicity, religion, and region.

Since Abiy Ahmed's regime came to power, especially in the past two years, the right to life and move freely, the rights of people under detention, economic and social rights, the rights of women and children, and the rights of refugees and inernally displaced people have all been under threat. In particular, citizens of Amhara identity are being uprooted from their homes and subjected to daily attacks by the regime in all parts of the country. In the past few years alone, over 100,000 people have been displaced under the pretext of development of corridors around Addis Ababa, alone. In addition, there are reports throughout the country that families of founders of cities were targetted under this pretext. More than a million Amharas have been displaced from the Oromia region alone, most of whom have been displaced and scattered widely, and those who have been placed in camps are exposed to hunger, disease, mental anguish, and various diseases.

#### Genocide Specifically Targeting The Amhara People

The Amhara people, who are in the midst of a war, are suffering severe human rights abuses due to the regime's tyranny.

The Amhara people, who have been subjected to extreme violence and abuse in a mechanized war from city to countryside, have found it a luxury to live peacefully. Their human rights have also been severely compromised.

The British international media BBC cited the European Center for Justice and Law, a non-governmental organization, in its ...

(Continues on Page 2)

- ❖ በትምህርት ተቋማት ላይ እየደረሰ ባለው ጥቃት ከ4.1 ሚሊዮን በላይ ህጻናት በትምህርት ገበታቸው ላይ መገኘት ያልቻሉ ሲሆን 5,231 (65.1%) ትምህርት ቤቶች ተዘግተዋል። ከተዘጉት ትምህርት ቤቶች ውስጥ 1,169 የሚሆኑት ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 830ዎቹ አገዛዙ ወታደራዊ ካምፕ አድርጎ የተጠቀመባው ናቸው፣
- ❖ እንደ አካባቢው የሰብዓዊ ዕርዳታ አስተባባሪዎች ግምት በመቶዎች የሚቆጠሩ በረሃብ እየሞቱ ባሉበት የአማራ ክልል ሕይወት አድን ሰብዓዊ ዕርዳታ ለሚያስፈልጋቸው 2 ሚሊዮን ለሚጠጉ ጉዳተኞች ተገቢው ዕርዳታ እየቀረበ አይደለም። በዚህም ምክንያት አይና ቡግና፣ ዳውንት፣ መና መቀጠዋ፣እብናት፣ ላይ ጋይንት፣ ምስራቅ በለሳና ጃናሞራ ወረዳዎች ከፍተኛ የሆነ የምግብ እጥረት ተከስቶ ይገኛል፤

## መሰረታዊ የግብዓት አቅርቦትን መከልከልና የህዝብ አገልግሎትን ማስተጓጎል

- ❖ የአብይ አሕመድ አገዛዝ በንፁሃን ላይ ከሚያካሂደው ጅምላ ጭፍጨፋ በተጨማሪ ፋኖ በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች ህዝቡ በፋኖ ላይ ቅሬታ ሊፈጥር ይችል ይሆናል በሚል የቂል እሳቤ የገበያ ምርቶችን እንዳይደርሱ የማስተጓጎል ስራ እየሰራ ይገኛል፣
- ❖ ፋኖ በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች ህዝቡን ለማሳቀቅ ትራስፖርትና ግብዓቶችን እየከለከለ ይገኛል። በዚህም ምክንያት ታካሚዎች ወደ ሆስፒታል እንዳይደርሱ፣ ከህፃናት ምግብ ጀምሮ መሰረታዊ የፍጆታ እቃዎች፣ የግብርና ግብዓቶች ለህዝቡ ተደራሽ እንዳይሆኑ እንዲሁም ማህበረሰቡ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ መስራት እንዳይችል የትራንስፖርትና የግብዓት ክልከላ እያደረገ ይገኛል።
- ❖ የአገልግሎት ተቋማት በተለይም ኔትወርክ፣ መብራት፣ ውኃ፣ ባንክና የመሳሰሉት ተቋማት ፋኖ በተቆጣጠራቸው ቀጠናዎች በአግባቡ እንዳይሰሩ እየተደረገ ይገኛል።

የአገዛዙ ሰራዊት በውጊያ ሽንፈት በሚገጥመው ወቅት በንፁሃን ላይ ከሚያደርገው የበቀል እርምጃ በተጨማሪ በህዝብ ተቋማት ላይ የማውደምና የዝርፊያ ስራ እየፈጸመ ይገኛል። በተለይም የተቋም ንብረቶችን ጭኖ መውሰድ ወይንም ማውደም፣ የመብራት መስመሮችን ማበላሸትና የጥገና አገልግሎት እንዳያገኙ መከልከል የዘወትር ተግባር ሆኖ ቀጥሏል።

## አፋሕድ ለዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎች ያለው አቋም

አፋሕድ በዓለም-ዓቀፍ ደረጃ የጸደቁ ሰብዓዊ መብቶችን፣ ዓለም-ዓቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች የሚያከብርና ለተፈጻሚነታቸው ተባባሪ እንደሚሆን በተደጋጋሚ መግለጹ ይታወቃል። የትግላችን መነሻ በማንነታችን የሚደርስብንን መንግስት መር ጥቃት ማስቆም፣ ፍትህ ማግኘት፣ እኩልነትና በሰላም ሰርቶ መኖርን ከመሻት ጋር የተያያዘ ሲሆን የእነዚህ መብቶች መከበር የትግላችንና የድርጅታችን ግቦች ሆነው በማኒፌስቶ ጭምር በግልጽ ተቀምጠው ይገኛሉ። በተለይም በዓለም አቀፍ ደረጃ የጸደቀውን Universal Declaration of Human Rights እና በአፍሪካ አህጉራዊ ይዘት ያለውን African Commission for Human and Peoples' Rights ያለምንም መሸራረፍ ተግባር ላይ እንዲውል አፋሕድ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይሰራል።

## አፋሕድ በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች ለመብቶች መከበር የሚኖረን ሚና

አፋሕድ በማንነት ላይ የተቃጣን ጥቃት በዘላቂነት ለማስቆምና የዜጎችን ሰብዓዊ መብት ለማስከበር እየታገለ ያለ ድርጅት እስከሆነ ድረስ ዜጎችን ስለ ሰብዓዊ መብት ምንነት እና የሰብዓዊ መብት አያያዝ በተመለከተ በባለሙያዎች ሰነድ አዘጋጅቶ ከማስተማሩም በላይ ከሌሎች አጋር አካላት ጋር በጥምረት የሚሰራ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን። በተለያየ ምክንያት ከመኖሪያ ስፍራቸው ለተፈናቀሉ እንዲሁም የተለያዩ ዓይነት ጉዳቶች ለደረሱባቸው ዜጎች ሰብአዊ እርዳታ ለሚያደርሱ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና የተሰጣቸው ተቋማት ሠራተኞች ደህንነታቸው እንዲጠበቅና ሰብዓዊ መብታቸው እንዲከበር በትኩረት መስራት እንዳለበት አፋሕድ በጽኑ ያምናል። ይህንን ሰብዓዊ መብት ከማክበርና ከማስከበር አንፃርም በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ ላይ በግልጽ የተቀመጠ ሲሆን የሰብዓዊ መብት ጥሰት ፈፅመው በሚገኙ አባሎቹ ላይም በከፍተኛ የዲስፕሊን ጥሰት የሚያስከስስ ወንጀል ሆኖ ተቀምጧል። ለተግባራዊነቱም ተግቶ ይሰራል።

## ለሰብዓዊ-መብቶች መከበር ከቀጠናዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም-ዓቀፍ ተቋማት ጋር በጥምረት መስራት የሚኖረው ፋይዳ

ስለሰብአዊ መብቶች የመሟገት መብት መጎልበትና ጥበቃ ማግኘት በአለም አቀፍ ደረጃ አድጎ መሪ ቃል ሆኗል። ይሁንና ለመብቶች መከበር እና ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት በተለያዩ ሕጎች እና ቃል ኪዳኖች የተጠቀሱትን ያህል በተግባር ያለው ትብብር እና በጋራ የመሥራት ባህል የጎላ አይደለም። በመሆኑም የሰብአዊ መብት ጉዳዮች እውቅና እንዲያገኙ ብሎም ባለድርሻ አካላት በአደባባይ መልስ እንዲሰጡ ለማድረግ አንዱ ወሳኝ መንገድ ከአለም-ዓቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብት ተቋማት ጋር ቁርኝት መፍጠርና ተናቦ መስራት መሆኑን አፋሕድ ያምናል። ለዚህም ስኬት የድርጅታችን ማህበራዊ ዘርፍ መምሪያ ኃላፊነት ወስዶ አፋሕድ በተቆጣጠራቸው ቀጠናዎች ያሉ አስተባባሪዎችና በየደረጃው ያሉ የዘርፉ አመራሮች ግንዛቤ ተፈጥሮላቸው ለሰብዓዊ ጥበቃና ድጋፍ ከሚንቀሳቀሱ የድርጅት አካላት ጋር በትብብር እንዲሰሩ አቅጣጫ ተቀምጧል።

በጥቅሉ በኢትዮጵያ በተለይም ከ2 አመት በላይ በጦርነት ውስጥ ባለው የአማራ ክልል የዜጎች ደህንነት በእጅጉ አደጋ ውስጥ ወድቋል። ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስና ወጥቶ መመለስ ከፍተኛ ስጋት ሆኖ ቀጥሏል። የዜጎች ኡኡታና ጩኸት ሳይሆን ስልጣኑና የግል ክብሩ የሚያስጨንቀው አምባ ገነን የሆነው የአብይ አሕመድ አገዛዝ በከባድ መሳሪያ በሚያደርገው የጅምላ ጥቃት ዜጎች በየቀኑ ህይወታቸው እየተቀጠፈ ይገኛል። በአገዛዙ የጸጥታ መዋቅር ስር ያሉና የጦርነቱን ግርግር እንደመልካም አጋጣሚ ተጠቅመው የሚንቀሳቀሱ ሽፍቶች በየአካባቢው በንጹኃን ላይ አልፎም ለሰብዓዊ ድጋፍ በሚንቀሳቀሱ አካላት ጭምር የከፋ ጥቃት እየተፈጸመ ይገኛል። ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ የመጣውን ይህን አሳሳቢ ጉዳይ ማስቆም የሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነት ነው። በተለይም የአብይ አሕመድ አገዛዝ በንፁሃን ላይ የሚያካሂደውን ጅምላ ጭፍጨፋ፣ በህዝብ ተቋማት ላይ የሚደረግን የማውደም ስራ እንዲሁም ፋኖ በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች ለማህበረሰቡ አንገብጋቢ የሆኑ የዕለት ፍጆታዎች፣ አገልግሎቶች፣ ሰብዓዊ እርዳታዎች ተደራሽ እንዳይሆኑና ህዝቡን ለመበቀል የሚደረግ ክልከላ በአስቸኳይ እንዲቆም ለዓለማቀፉ ማህበረሰብ ጥሪያችን እናቀርባለን።

አፋሕድ የህዝብን ጥያቄ አንግቦ አላማ ይዞ እንደሚንቀሳቀስ ድርጅት ይህ ጉዳይ በእጅጉ እያሳሰበው በመሆኑ የጦርነቱ ተሳታፊ ያልሆኑ ዜጎችን መብትና የህዝብ ተቋማትን ለመጠበቅ ከምንጊዜውም በላይ ትኩረት ሰጥቶ የሚንቀሳቀስ ሲሆን በሰብዓዊ መብት ጥበቃና የአስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ የሚንቀሳቀሱ ባለድርሻ አካላት ጉዳዩን ትኩረት ሰጥተው እንዲንቀሳቀሱ ጥሪ እያቀረብን ዜጎችንና የሰብዓዊ ድጋፍ አቅራቢ ድርጅት ሰራተኞችን ደህንነት ለመጠበቅና በትብብር ለመስራትም ዝግጁ መሆናችንን በሙሉ ልብ እንገልጻለን።

ድል ለአማራ ህዝብ!

ሰላም ለኢትዮጵያ!

ረቡዕ ነሐሴ ፳፩ ቀን ፳፻፲፯ ዓ.ም.
ኢትዮጵያ።

(Editorial, continued from Page 1)

2024 report, "The Silent Suffering of the Amhara People in Ethiopia" detailing the atrocities committed in and outside the region since 2018 E.C. The media reported that thousands of Amharas have been killed in Oromia State and other parts of the country.

In addition, the Amhara Association in America, AAA has identified the following: in its investigations: drone strikes have killed many innocent civilians who were not involved in the war, such as in markets, schools, and health centers. For example, from September 25 to December 30, 2024, 99 drone strikes and airstrikes in 46 districts of the Amhara region killed 390 people, injured 135, with a total casualty of 525 people. This damage occurred in three months, and it is not difficult to estimate the damage caused during the two-year war.

Also, in a previous report (July 2024), the AAA had listed the following damages, atrocities, and casualties in the Zones of the Amhara region where the report was compiled:

- ❖ 269 people were raped, most of whom were young girls and women, with a small number of male priests and young men also being victims.
- ❖ more than 4.1 million children are out of school due to ongoing attacks on educational institutions, and 5,231 (65.1%) schools have been closed. Of the closed schools, 1,169 have been severely damaged, 830 of which are used by the regime as military camps.
- ❖ the nearly 2 million people in need of life-saving humanitarian assistance in the Amhara region, where hundreds are dying of hunger, are not receiving adequate assistance. As a result, severe food shortages have occurred in the districts of Ayna Bugna, Daunt, Mena Meketewa, Ebnat, Lay Gaynt, East Belessa and Janamora.

## Basic Supplies And Disruption Of Public Services

In addition to the mass killings of innocent people, the Abiy Ahmed regime is also working to prevent the delivery of market products in areas controlled by Fano, under the false hope that the public might resent the Fano. With this false hope the regime is restricting transportation and resources to the people in the areas under the control of Fanos. It is restricting transportation and resources to prevent patients from reaching hospitals, preventing the people from accessing basic necessities and supplies to agricultural inputs, and preventing the community from moving from place to place.

Service facilities, especially network, electricity, water, banking, and other institutions, are being prevented the regime from functioning with full capacity in areas controlled by Fano.

In addition to its retaliation against innocent people when faced with defeat in battles, the regime's army is also carrying out acts of destruction and looting against public institutions. In particular, the seizure or destruction of institutional assets, the...
(Continues on Page 3)

(Contiinued from Page 2)

damage to power lines, and the denial of access to maintenance services have continued to be regular activities of the regimes army.

### AFPO's Position On International Human Rights Law

AFPO has repeatedly stated that it respects and supports internationally recognized human rights and international human rights instruments and that it will cooperate in their implementation. The basis of our struggle is related to the desire to stop the state-directed attacks on our identity, to achieve justice, equality and to live in peace, and the respect for these rights is clearly stated in our manifesto. In particular, AFPO pays special attention to the implementation of the internationally recognized Universal Declaration of Human Rights and the African Commission for Human and Peoples' Rights.


### Our Role In Ensuring Respect For Rights In Areas Controlled By The AFPO

As an organization that is fighting to stop the attacks on our identity and to protect the human rights of our citizens, we would like to state that we work in collaboration with other partners, in addition to preparing and educating citizens about the nature of human rights and human rights management through expert trainings and flyers. We firmly believe that the safety of the workers of internationally recognized institutions that provide humanitarian assistance to citizens who have been displaced from their homes for various reasons and who have suffered various types of harm should be protected and their human rights respected. In terms of respecting and protecting this human right, it is clearly stated in the organization's bylaws, and it is also a crime that can be punished with severe disciplinary action against its members who commit human rights violations. We also work hard to implement it.

### The Benefits Of Working In Partnership With Regional, Continental And International Institutions To Promote Respect For Human Rights

The promotion and protection of human rights has become a global issue. However, the practical implementation of the principles mentioned in various laws and treaties to achieve respect for rights and sustainable solutions is not enough. Therefore, AFPO believes that one of the important ways to ensure that human rights issues are recognized and that stakeholders are held accountable is to establish and work in partnership with international and regional human rights institutions. To achieve this, the Social Affairs Department of our organization has taken responsibility and has set a direction for the coordinators and sector leaders at all levels in the areas under AFPO's control to work in collaboration with organizations working for human protection and support.

In Ethiopia in general, and especially in the Amhara region, which has been at war for more than 2 years (and parts of it for more than 4 years), the security of citizens is in grave danger. Moving from place to place remains a major challenge. The Abiy Ahmed regime, which is not concerned with the citizens' freedom and their sufferings, but with its power and personal cult, is destroying the lives of citizens every day with heavy weapons. Bandits operating under the regime's security structure and taking advantage of the chaos of the war as a good opportunity are carrying out serious attacks on civilians in various areas, including attacks agains those working for humanitarian aid. It is the responsibility of all stakeholders to stop this serious issue that has been worsening from time to time. In particular, we call upon the international community to immediately stop the Abiy Ahmed regime's massacre of innocent people, the destruction of public institutions, and the denial of access to essential daily necessities, services, and humanitarian aid.




As an organization that works with the public's demands and aims, AFPO is deeply concerned about the above metioned human rights issues, and therefore, it is working more than ever to protect the rights of civilians and public institutions. Finally, we call on stakeholders involved in human rights protection and emergency assistance to pay special attention, and express our readiness to work together to protect the safety of citizens and staff of humanitarian aid organizations.

**Victory to the Amhara People.**

**Peace for Ethiopia**

**August 27, 2025**

**Ethiopia**